# “የቋንቋ አገልግሎት ማግኘት” የእርስዎ የመጠቀም መብት ነው!

የኮሎምቢያ ክልል ውስን የእንግሊዘኛ ቋንቋ የሚናገሩ ወይም ምንም መናገር የማይችሉ ሰዎችን መብቶች ይጠብቃል። እ.ኤ.አ. በ2004 በወጣው የዲ.ሲ. ቋንቋ ድንጋጌ መሰረት እንግሊዘኛ ቋንቋን መናገር፣ ማንበብ ወይም መጻፍ የማይችሉ የኮሎምቢያ ክልል ነዋሪዎች በሕዝባዊ አገልግሎቶች፣ መርሐ-ግብሮች እና ስራዎች ውስጥ እኩል የመጠቀም እና የመሳተፍ እድልን የዲ.ሲ. አስተዳደር እንዲሰጣቸው ያስገድዳል።

ከዲ.ሲ. አስተዳደር አገልግሎት ካስፈለገዎ እና እንግሊዘኛ መናገር፣ ማንበብ፣ መጻፍ ወይም መረዳት የማይችሉ ከሆነ፣ የሚከተሉት መብቶች አሎዎት፡

## እርስዎ ምንም ወጪ ሳያወጡ ግልጋሎት በአስተርጓሚ እንዲሰጡዎት መጠየቅና ማግኘት፦

የዲ.ሲ. አስተዳደር እርስዎን በግል ለመርዳት ብቁ የሆነ አስተርጓሚ እንዲቀርብልዎ ያደርጋል ወይም በግል አስተርጓሚ የማይገኝ ከሆነ የስልክ የትርጉም አገልግሎት የሚሰጥ ባለሙያ ያቀርብልዎታል።

## እርስዎ ምንም ወጪ ሳያወጡ አስፈላጊ ሰነዶች በእርስዎ ቋንቋ እንዲዘጋጁልዎ መጠየቅና ማግኘት፦

የዲ.ሲ. አስተዳደር ተወካዮች ማመልከቻ፣ ማስጠንቀቂያ፣ የአቤቱታ ቅጾች የመሳሰሉትን የተለያዩ የተተረጎሙ ሰነዶችን የሚሰጡ ሲሆን፣ እነርሱ በስፋት የሚያገለግሉት ህዝብ በሚናገራቸው ከእንግሊዘኛ ውጪ በሆኑ ቋንቋዎች የሚገኙ ሰነዶችን ያድላል።

## አቤቱታ ማቅረብ፦

ከአንድ የዲ.ሲ. አስተዳደር ተወካይ በቋንቋዎ አንድ አግልግሎት የመጠቀም  እድል ማግኘት ካልቻሉ፣ ተወካዩ ምናልባት የዲ.ሲ.ን በቋንቋ የመጠቀም ህግን የማይፈጽም ሊሆን ይችላል። ስለዚህ እባክዎ ይህን ጉዳይ ለዲ.ሲ. ቋንቋ አጠቃቀም ፕሮግራም በሠብዓዊ መብቶች ጽ/ቤት በኩል በስልክ ቁጥር (202) 727-4559 ደውለው ያሳውቁ። አገልግሎቶችን በቋንቋዎ የማግኘት መብት እንዳለዎ ያስታውሱ።

**የዲ.ሲ. የሠብዓዊ መብት ቢሮ**

**አድሪየን ኤም. ፌንቲ**
**ከንቲባ**

ከዚህ በታች ያለውን ካርድ አውጥተው ከአንድ የዲ.ሲ. አስተዳደር ተወካይ አገልግሎት ለማግኘት ሲጠይቁ ይጠቀሙበት። ይህን ካርድ ሁልጊዜም ከእጅዎ አይለዩት።

**አማርኛ እናገራለሁ**

**የቋንቋ እርዳታ ያስፈልገኛል። እባክዎ በሰነዱ ውስጥ ስለምናገረው ቋንቋ እንዲሁም አስተርጓሚ የምፈልግ ስለመሆኔ ፋይሌ ውስጥ ያስቀምጡ።**

የኮሎምቢያ ክልል ህግ የዲ.ሲ. አስተዳደር ተወካዮች በመርሐ-ግብሮቻቸው ውስጥ **እኩል ተጠቃሚነትን** እንዲያረጋግጡ ያዛል። ለበለጠ መረጃ ወይም አቤቱታ ለማቅረብ በሚከተለው አድራሻ ያግኙን።

**የዲ.ሲ. የሠብዓዊ መብት ቢሮ**
**(202) 727-4559**
www.ohr.dc.gov